# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞ ቅጽ 41 ቁ. 1** **መስከረም 2013 ዓ.ም**


## ከታገሉ ፀንቶ፤ የጀግኖችን ገድል አድምቆ!!

የነዚያ ጀገኖች ኢትዮጵያውያን የአርበኝነት ትግል ረዥም፤ መራራና ውጣ ውረድ የበዛበት ቢሆንም፤ ሕዝባዊ የትግል ወኔው ዛሬም ሳይቋረጥ ከትውልድ ወደትውልድ ለመሸጋገሩ ቋሚ ምስከሩ አሁንም የአገር አንድነትንና ሉዓላዊነትን፣ ማኅበራዊ ፍትኅን እንዲሁም ሥልጣን ከሕዝብ የሚመነጭበትን ዴሞክራሲያው ሥርዓት ዕውን ለማድረግ የሚካሄደው ትግል መቀጠሉ ነው። ይህ ዘመናትን ያስቆጠረውና የአገር አንድነትና የወገን ፍቅር በሚያንገበግባቸው የነቁ አገር ወዳድ ምሁራን የተጀመረው አገር በቀል ትግል እንደ ትንታግ እያደር እምቅ ጉልበትን እያካባተ ፤ እየሰፋና እየተጠናከረ ረዥሙን ሕዝባዊ ጉዞን በራሱ ሂደት የተጓዘ፤ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች ተከታዮችን ደጋፊዎችንና አድናቂዎችን እያሰባሰበ፤ በፍልስፍናው ጥራትም ሆነ በማኅበራዊ አደረጃጅቱ መሠረተ ሰፊ ሕዝባዊ ገጽታዎችን በመላው የአገሪቱ ክፍሎች እየገነባ የመጣ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመሆኑ ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው።

ከፋሽስት ወረራ በፊት የኋላቀር መኳንንት ግፊትን በመቋቋም በተለይም ለዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት የታገሉት የለወጥ አራማጆች፤ ወቅቱ የጠየቀውን የትግል መሥዋዕት በመክፈል የራሳቸውን የትግል ታሪክ አሻራ ትተውልን አልፈዋል። የኢጣሊያን ፋሽስቶችን የግፍ ወረራ በድል አድራጊነት የተወጡት አርበኞች በድሉ ዋዜማ ኢትዮጵያ እንደነ ጃፓን አሊያም እንደነ ፈረንሳይ፣ …ወዘተ በ"ሪፓብሊክ" ሥርዓት ትተዳደር፤ ከኋላቅርነት ትላቀቅ በእድገትና ልማት ጎዳና ትራመድ ብለው በመጠየቅ ለፊውዳላዊውና መለኮታዊው ፍጹማዊ የዘውድ አገዛዝ አማራጩን ጠቁመዋል። በ1953 ዓ.ም ታኅሣሥ 5 ቀን ንጉሠ ነገሥቱን ለጥቂት ቀናትም ቢሆን አውርደው "ፍትህ በኢትዮጵያ ይበየን" ያሉት ወጣት ምሁራንና የጦር መኮንኖች ራሳቸው የእሳት ራት ቢሆኑም ፊውዳላዊውን ሥርዓት ለመጣል "ሕዝባዊ አደረጃጃት" የማይታለፍ ግዴታ መሆኑን እንዲጠይቅና እንዲረዳ ለቀጣዩ ተራማጅ ትውልድ ዓብይ አስተምሮትን ትተው አልፈዋል። ከዚያም እስከ የካቲት 1966 ድረስ በአገር ውስጥና በውጪ የተደራጁት ወጣት የኢትዮጵያ ምሁራን ግፍና በደል፣ ረሃብና ቸነፈር የበረታበት ወገናቸውን ለመታደግ በተበታተነ መልክ ይካሄድ ለነበረው ትግል በበኩላቸው ርእዮተ- ዓለማዊ መሠረትና ድርጅታዊ ሕልውናን ለማላበስ ሳይታክቱ ጥረዋል።

በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲ ባህል አለመኖር ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ ውስጥ የበቀሉና ፍትኅና ርትዕ ፈላጊ የነበሩትን ተራማጅ ምሁራንን ሲያሳስብና ሲያስጨንቅ ቆይቷል። በወቅቱ የነቁ ወጣት ተራማጅ ምሁራን መሠረታዊ የሆኑ የአገሪቱን ኤኮኖሚያዊ ማኅበራዊና ፖሊቲካዊ ችግሮችን የማጤን ክህሎታቸውን በተጨባጭ በአገራቸው ከሚታየው የፍትኅ መዛባትና አድሎ ጋር በማዛመድ የሚወዷት ሀገራቸውን ኋላቅርነትና የወገናቸውን በደል በሚችሉት ዜዴ ሁሉ ለማንሳት ለመጠቆምና በአደባባይ ጭምር ለማስተጋባት ሞክረዋል ።

እነዚህ ተራማጅና ለውጥ ፈላጊ ወጣት ምሁራን መሠረታዊ የሆኑ የሀገሪቱን ጥያቄዎችን የመረዳትና የማንሳት አቅም ያጎለበቱ ቢሆንም ተቃውሟቸውን ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ ለማካሄድ መቸገራቸው አልቀረም። ለሀገራቸው ትልቅ ተስፋንና ምኞትን የሰነቁ ብሩህ ዓእምሮና ችሎታ የነበራቸው ሩቅ አሳቢ ወጣት ምሁራን የነቀሱት አገራዊ ራዕይ ወደፊት ይራመድ ዘንድ ከተማሪዎች ማኅበር እንቅስቃሴ ባሻገር የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ወደፊት ለማስቀጠል ድርጅት መፍጠርና ትግሉንም በተደራጀና በተቀናጀ መልክ ማራመድ እንደሚያስፈልግ በማመን ኢትዮጵያዊ፤ ሀገራዊና ኅብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅት መፍጠር ለነገ የማይባል ተግባራቸው መሆኑን በሚገባ ተረዱ።

እነዚህ ጥቂት የድርጅትን ጥቅምና የመደራጀትን አስፈላጊነት የተገነዘቡት የዚያ ትውልድ አባላትም በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ተመሳሳይና መሠረታዊ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸውን ተራማጅ ኢትዮጵያዊ ቡድኖችን በመገናኘትና ተከታታይ ውይይቶችን በማድረግ አስፈላጊውን የፖለቲካ ድርጅት ምሥረታ ቅድመ ዝግጅት የሚያደርግ በህቡዕ የሚንቀሳቀስ የአደራጅ ኮሚቴን አቋቋሙ። ከዚያም በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ በፖለቲካ አመለካከትና በዓላማ አንድነት ላይ ተመሳሳይ አመለካከት ካላቸው ለአገራቸው አንድነትና እደገት ፤ ለወገናቸው ፍትኅና ዴሞክራሲ የሚመኙ ታጋይ ኢትዮጵያዊያን የሚያሰባስብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያና አገራዊ የሆነ ብሩህ ተስፋንና ራዕይን የሰነቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ድርጅት (ኢሕአድ) የሚል መጠሪያ የነበረውን የፖለቲካ ድርጅት የዛሬ አርባ ስምንት ዓመት በሚያዚያ ወር 1964 ዓ.ም በጀርመን ሀገር በበርሊን ከተማ መሰረቱ።

ይህ በአገራችን የፖለቲካ ትግል ታሪክ ፋና ወጊ፤ ተስፋን ፈንጣቂ የሆነው የፖለቲካ ድርጅት የትግል አድማሱን በማስፋትና ራሱን ቀስ በቀስ በማጎልበት ለለውጥ ፍለጋ ይተጋ የነበረውን የኅብረተሰብ ክፍል በመያዝ፤ በወቅቱ አገሪቱ የነበረችበትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ከዓለም አቀፉ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ኅበረተሰቡን ለማንቃትና ለማደራጀት የሚያስችሉ የተለያዩ የትግል ስልቶችን በመቀየስ ራሱን በህቡዕ ሲያደራጅና ሲያጠናክር ድርጅታዊ መዋቅሩን በተለያዩ የኅብረተስብ ክፍሎች ውስጥ ሲዘረጋ ቆየ ።

የሀገሩ ኋላቀርነት ያንገበግበው የነበረው የተማረው ተራማጅ ወጣት ትውልድ በወቅቱ በአገራችን ጎልቶና ፈጦ ይታይ የነበረውን የፍትኅ መዛባት፤ አድሎና በደል እንዲሁም በዓለም ደረጃም ተንሰራፍቶ የነበረውን የቅኝ ግዛትንም ይቃወም የነበረ ትውልድ ነው። ይህ ታላቅና ጀግና ብሩህና አስተዋይ ዓእምሮን የታደለው ትውልድ እይታው የሰው ልጆች ሁሉ በተፈጥሮ እኩል ናቸው፤ በአንድ ቦታ ያለ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሁሉም ቦታ እንደተፈጸመ ተደርጎ መታየት አለበት በሚል ቅን አስተሳሰብ የተመሰጠ፤ ለሰው ልጆች ሁሉ መብት መከበር የቆመና የታገለ፣ የህይወት መሥዋዕትነትንም ጭምር የከፈለ አስተዋይ ትውልድ ነበር።

የለውጥ ፈላጊው ወጣት ትውልድ አባላት የተበደለውን ሕዝብ ብሶት በማስተጋባት በሀገራቸው ትምህርትንና የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ፣ ሁሉም ዜጋ የሥራ ዕድል የሚያገኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር፣ የዜጎችን መብትና ጥቅም በእኩልነት ለማስከበር፣ ብዝበዛንና ጭቆናን ለማስወገድ፣ ትምክህተኝነትንና ጠባብ ብሔረተኝነትንም በመቃወም ፍትኅና ርትዕ ለሰፈነባት፣ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት ለሚኖሩባት፤ አንድነቷና ሉዓላዊነቷ ለተከበረ ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ዕውን መሆን መታገላቸውና ወደር የማይገኝለትን መሰዋዕትነት መከፍላቸው የሕዝብ ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ ከዚያ ትውልድ ማለትም ከኢሕአፓ በተፃራሪ የቆሙት ሁሉ የተቀበሉትና ያመኑት ሐቅ ነው።

ኢሕፓን የመሠረቱትም ሆነ በሂደት ድርጅቱን የተቀላቀሉት አባላቱና ደጋፊዎቹ ለሚወዷት እናት አገራቸውና ለሚያከብሩት ሕዝብ ሲሉ ምትክ የማይገኝለትን ክቡር ህይወት ገብረዋል፡፡ ኢሕአፓን በመቀላቀል የታገለና እየታገለም ያለው ይህ ኢትዮጵያዊ ጀግና ትውልድ ያለጥርጥር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ፍቅር፤ ለፖለቲካ ራዕዩ መሳካት ባደረገው ትግልና በተጨባጭ በከፈለው መሥዋእት የገለጠና ዛሬም ይህንኑ ገድል በተግባር እያሰቀጠለ ያለ አኩሪ የጽናትና የቆራጥነት ምሳሌ የሆነ ትውልድ ነው።

የእንቅስቃሴው አባላት የነበሩት አንዳንዶቹ በሥልጣን ተደልለው ለአምባገነኖች ስላደሩና ስለተባበሩ ወይንም በእንቀስቃሴው ምንም ሚና ሳይኖራቸው አሁን ያላቸውን የተዛባ ፖለቲካ ቀባብቶና አሳምሮ ለማቅረብ "የተማሪው እንቅስቃሴ የወለደን ነን" የኢሕአፓ መሥራች ፤ የነቃን የበቃን ነን የሚሉ አደርባዮችና ሀሳዊ መሲኅዎች በፖለቲካው መድረክ ብቅ ብቅ ስላሉ የነዚያ ብርቅዬ ጀግኖች አኩሪ ታሪክ ሊጎድፍ ወይ ሊካድ የሚገባው አይደለም።

በ1966ቱ የካቲት ሕዝባዊ አብዮት ወቅት በዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ዙሪያ የተካሄደው መራራ ትግል አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆችና የሕዝብ ጠላቶች እንደሚሉት "ሁሉም አንድ ነበሩ!" እያሉ ሊያግቸለችሉና ጥላሸት ሊቀቡ እንደሚሞክሩት አልነበረም። ዛሬም አይደለምም።

ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም! ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ! ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ ይመለስ! ...ወዘተ፤ ብለው የታገሉት የኢሕአፓና የሕዝብ ወገኖች ተቃርነው የቆሙት በኢትዮጵያ ትቅደምና በሶሻሊዝም ሽፋን ዲሞክራሲን ለመገድብ ራሱን ያደላድል የነበረውን የምርጥ መኮንኖችን አገዛዝ በመደገፍ ሲንቀሳቀሱ ከነበሩት ጋር ነው። በዚህ መሠረታዊ የልዩነት ዙሪያ የተደረገውን ትግል ታሪክ መካድና ልዩነቶቻቸው በ"ቸ ና በሸ" ነበር በማለት እውነታውን አጣመውና አራክሰው ለማቅረብ የሚሞክሩትን ሁሉ "ከተበደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ለመቆም ምነው አልደፈራችሁ ? መስመራችሁ ከየት ነበር?" ብሎ መጠየቅና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሂሳባቸውን እንዲያወራርዱ ማድረግ የዛሬው ለውጥ ፈላጊ ትውልድ ሀገራዊ ግዴታ ነው ብለን እናምናለን ።

በአምባገነኖች የብዕርና የገንዝብ ድጎማ እየታገዙ የልበወለድ ታሪክ እንዲጽፉና እንዲያሰራጩ ተተኪው ትውልድን ኢላማ ያደረገ፤ ትውልድ ይቅር የማይለው ወንጀል አየፈጸሙና እያስፈጸሙ ይገኛሉ። ኢሕአፓ ከተመሠረተበት ከሚያዚያ 1964 ጀምሮ ያነሳቸው የሕዝብ ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ አላገኙም። የኢሕአፓ ትግል አልፋና ኦሜጋው የሕዝብን ጥቅም መጠበቅና ፍላጎቱን ማሟላት ፤ እንዲሁም ለአገሪቱ ሰላምንና እድገትን ማረጋገጥ እንጅ የሚፈሩቱና የሚጠሉት እንደሚያናፍሱት አይደለም። ይህንን አኩሪና ምትክ የማይገኝለትን የትግል ታሪክና ገድል ምርቱን ከገለባው መለየት፤ መከላከልና መጠበቅ የሚገባው የዛሬው አገር ወዳድ ፍትህና ርትዕን ናፋቂ ወጣት ትውልድ ነው ብለን እናምናለን።

ከላይ ለማስፈር እንደሞከርነው የዚያ ትውልድ አባላት በቡድን በድርጅትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ታላቅ ሚናን ተጫውተዋል። የሕዝብን ትግል ሰፋትና ጥልቀት ጥራት በመስጠት፤ የአምባገነኖችን ተንኮልና ሴራ በማጋለጥ፤ ሕዝቡን በማንቃትና በማደራጀት፤ ...ወዘተ ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያደረጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። ለውጥ አቀንቃኝ የነበረው ተራማጅ ምሁር በውስብስብና በፈጣኑ ፖለቲካዊ ሂደት በኃይል አሰላላፍና በአቋም ልዩነት ክፍፍላቸው እየተጠናከረ ቢመጣም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በፈነዳበት ወቅት የምርጥ መኮንኖች አገዛዝ እስከተሰየመበት ድረስ በአብዛኛው መልኩ ሕብረትን ባለየ ትግል ለሕዝብ መብት ታግለዋል። ይህንን የተራማጆች ሚናና ድል አንዳንድ ክፍሎች

ሊከዱ ሆነ ሊያናንቁ ስለሚጥሩ በእኛ በኩል የትግላችን የታሪክ አካል በመሆኑ ለሐቁ ሥፍራ ሰጥቶ ማለፍ ዛሬም ተገቢ ነው ብለን እናምናለን።

መላውን የኅብረተሰብ ክፍል በኅብረት ያንቀሳቀሰው የ1966ቱ የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት መሠረቱ የዲሞክራሲ ጥያቄ እንደነበር ይታወቃል። በወቅቱም ሕዝቡን ሊያሰባስቡ፤ ሊያደራጁና ሊያታግሉ የሚችሉ ሕዝባዊ መፈክሮች ተረቀው በስፋትና በጥልቀት ተብራርተው በሁሉም  የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ተጨብጠው ነበር ለማለት አይቻልም። ነገር ግን ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፤ መሬት ለአራሹ ይሁን፤ ሕዝብ መሪዎቹን ይምረጥ፤ የሠራተኛና የሙያ ማህበራት በነፃ ይደራጁ፤ የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የፆታ እኩልነት ይስፈን፤ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ለሁሉም ይሰጥ፤ የታሰሩ የህሊናና የፖሊቲካ እስረኞች ይፈቱ፤ የኤርትራ ጥያቄ በሰላምና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ፤ …ወዘተ የሚሉትና ኋላም ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም በማለት ሲስተጋቡ የነበሩት መፈክሮች የብዙኀን ድምጽ ከመሆናቸውም ሌላ በወቅቱ መሠረታዊ የሆነው የዴሞክራሲ ጥያቄ አካል እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው። እስከዛሬም ድረስ እነዚህ መሠረታዊ  የሕዝብ ጥያቄዎች በአግባቡ ባለመፈታታቸው/ባለመመለሳቸው የተነሳ ችግሮቻችን ከትውልድ ወደትውልድ እየተሸጋገሩ ጥያቄዎቹ መፍትኄ እንዲያገኙ የሚደረገው ትግልና የሚከፈለው መስዋዕትነት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሰጋ  ዛሬም እንደቀጠለ ይገኛል።

ለውጥ ፈላጊው ትውልድ የኢትዮጵያን ሕዝብ የፖለቲካ ንቃትና ትግል የድርጅት ጥንካሬውን  ከፍ ወዳለ  ደረጃ ለማድረስና የሕዝቡንም የማይገረሰስ የሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ከአጽናፍ እስከ እስከጽናፍ እየተቀጣጠለ በመሄድ ላይ የነበረውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማስተሳሰር ጥረቶችን ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ከላይ የጠቀስነውን ኢሕአድ የተባለውን የደርጅት መጠሪያ በመቀየር በነሐሴ 26 1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ዓመት መባቻ ላይ “የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ” - ኢሕአፓ - በሚል  ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሥራት አለኝታና መከታ ለመሆን መዘጋጀቱን “ፍጹም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ህይወቴ፤ ጠላት ይፍራ ይሸበር የአድርባይ ቅስሙ ይሰበር፤ … ለማያጠረጥር ድሉ” በሚለው የድርጅቱ ሕዝባዊ መዝሙር አጅቦ የኢሕአፓን ይፋ መሆን የምሥራች አበሰረ።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተፈጠርው ኢሕአፓም በቆራጥ አባላቱ የዓላማ ጽናት ቆራጥነትና አይታክቴነት፤ በዓላማው ሕዝባዊነት የተነሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባዊ ድጋፍና ተወዳጅነት ለማግኘት በቃ። የሕዝብ አለኝታነቱን ጭቆናና ግፍን ግምባር ቀደም ሆኖ በመጋፈጥና ውድ ህይወቱን በመክፈል አረጋገጠ። በድርጅቱ ልሳን በዴሞክራሲያ አማካኝነትም የተበደለወንና የተገፋውን ሕዝብ ብሶት፤ ለቅሶና ዋይታ ሳያሰልስ እየነቀሰና እያጣቀሰ፤ መፍትኄዎችንና አማራጮችን እየጠቆመ በመቀስቀስ፤ በብዙሃኑ ልብ ውስጥ ሰረፀ። ልዩ የመጻፍና የማደራጀት ተሰጥኦና ችሎታ የነበራቸው የድርጅቱ አባላት ባደረጉት ያልተቋረጠ ጥረትና ትግልም  ኢሕአወሊ፤ ኢሴትድ፤ ኢላዓማ የኢጭወታድ፣ …ወዘተ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሳቸውን እውን አደረጉ። ሕዝባዊ ትግሉም ከፍ ወደአለ ደረጃ ተሸጋገረ።

የተለየዩ የህብረተሰብ ክፍሎችም የድርጅቱን (የኢሕአፓን) የትግል ጥሪ ተቀብለው ህዝባዊ አጋርነታቸውን በተግባር አስመሰከሩ። ለሙብት ለነጻነት ሲባል መከፈል ያለበትን መሥዋእትነትም በተግባር ከፈሉ። ዴሞክራሲያም ቀስቃሽነቷንና አደራጅነቷን በማጠናከር በስፋት በአማርኛ የጀመረችውን ህትመት በኦሮምኛ፣ በትግሪኛ፣ በወላይትኛ፣ በደራሳኛና በእንግሊዝኛ በሌሎችም ቋንቋዎች እየታተመች  በህዝብ ውስጥ በስፋት ትሰራጭ ጀመር።

አገዛዙ ከሚከተለው ፖሊሲና አሰራር ውጭ ሌላ አማራጭ መኖሩንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በስፋት ተረዳ። የትግል አጋሩንና የትግል ባላንጣውንም በሚገባ ለየ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ ነቃ ከዳር አስከዳር ተደራጀ። የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑንና ሞግዚት እንደማያስፈልገውም በማያሻማ ሁኔታ በየህዝባዊ መድረኮችና በየአደባባዩ በሚደረጉ ሠልፎች ላይ ሳይቀር አቋሙን ግልጽ አደረገ፣ ብሶቱን አስተጋባ፤ ቁጣውንም ገለጠ። የትግል ወዳጁንና ባላንጣውን በሚገባ ለየ። ኢሕአፓን በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ድጋፍ የተመለከተው ደርግ ተሸበረ ፤ አጃቢዎቹ የነበሩትም አድርባዮች ቅሥም ተሰበረ።

በወቅቱ ከሕዝቡ ህይወት ጋር መዋሃድ የጀመረው የነጻነት (የመጻፍ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ የመቃወም፣ ...) መንፈስ ደመና አንዣበበበት። የአፄው አገዛዝ አድርጎት የማያውቀውን አፋኝና የብዙሃኑን ሕዝብ ልሳን በአዋጅ ለጎመ ። በወቅቱ ደርግ ሥልጣኑንን መሉ በሙሉ በብቸኝነት ለመቆጣጠር ማቀዱን በመገንዘቡ ኢሕአፓ በልሳኑ በዴሞክራሲያ የደርጉ ሥርዓት ከአፄው አገዛዝ የባሰ ፈላጭ ቆራጭ መሆኑን አጋለጠ። ሕዝቡም አጥብቆ ሊታገለው እንደሚገባ የትግል ጥሪ አቀረበ።

ደርግም ሳይውል ሳያድር በኢሕአፓ ላይ የማጥፋት ዘመቻውን ከፈተ "ሞት ለኢሕአፓ!" "ቀይ ሽብር ይፋፋፍም!" ሲልም ፋሽስቱ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም በአደባባይ አጓራ። ጭፍጨፋውንም አካሄደ። የንፁሐን ደም በየአደባባዩ እንደጎርፍ ፈሰሰ። የኢትዮጵያ እናቶችም ሽማና ደረት በደም እንባ ራሰ። ኮሎኔሉ በዚህ አላበቃም ፈሪና ተጠራጣሪ ከመሆኑ የተነሳ የተለየ ሀሳብ የሚያነሱትንና የሚቃወሙትን የደርግ አባላት ሳይቀር አንድ ባንድ በየተራ ረሸነ። በመጨረሻም ሥልጣን በአንድ ግለሰብ እጅ ተጠቃላ ገባች።

በየካቲት 1966ዓ.ም. ሕዝቡ የጠየቀውና በርካታ ታጋዮች ህይወታቸውን የገበሩለት የመሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ (ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የመሆን መብት) ምላሽ ሳይገኝ ቀረ። የሕዝቡ ትግል መቀጠሉ የግድ ሆነ። ብዙሃኑ የተጨፈጨፉበት፤ የተሰደዱበትና የተጋዙበት ሕዝባዊ ትግል ግን በከንቱ ተዳፍኖ አልቀረም። የዚያ ትውልድ ጀግኖች የለኮሱት የነፃነት ችቦ ያነገቡት አገራዊ ራዕይ የአምባገነኖችን አገዛዝ መሠረት የሚንድ እምቅ ኃይልን አሠረፀ። ኢሕአፓን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠልና ለማጥፋት የተደረገው ዘመቻም በቆራጥ አባላቱና ደጋፊዎቹ ከሸፈ። ይባስ ብሎም ለተከታታይ አመፅ ምንጭ ሆነ። የፋሽስቶችና የጎጠኞች ያላባራ በትር የተፈራረቀበት የዚያ ትውልድ ትግል አናቱን ቢመታም አልተነቀለም። ሥሩም አልደረቀም። ይባስ ብሎ የአምባገነኖች የእገር እሳት የጎን አሾህ በመሆኑ ቀጠለ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታነቱንና መከታነቱን የበለጠ አረጋገጠ። የገባውንም የትግል ቃል ኪዳን ሳያጥፍ ዛሬም እነሆ ትግሉን በፅናት ቀጥሏል።

አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ዓመት ሲተካ ለአፍታ ቆም ብለን ያለፈውን ረዥሙንና መራራውን ሕዝባዊ ትግላችንን ስንገመግም በኢሕአፓ ላይ የዘመቱትን ክፍሎች ማንነት አበጥሮ ለሕዝብ በአደባባይ ማጋለጡ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን። ኢሕአፓን መሠረት ለማሳጣት፣ ለማጥፋት ሲሞክሩ የነበሩት ማንነት ሲመረመር ሁሉም በአቋሞቻቸው በቂ ምክንያቶች እንዳሉዋቸው ግንዛቤን ወስደናል። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ይከበር በማለቱና ለጥቅማቸው አለማደሩ ባዕዳን ጥቃት ሲሰነዝሩበት ቆዩ። አገር በቀል እንክርዳዶቹ ደግሞ የኢትዮጵያን ታሪክ በመሰረዝና በመደለዝ በፈጠራ ትርክታቸው በሕዝብ መሀል ጥላቻና እልቂት ተፈጥሮ የአገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ ለመጣል ሲሞክሩ በብርቱ

የተቃወማቸውና አጥብቆም የታገላቸው ኢሕአፓ በመሆኑ በዋና ጠላትነት ፈርጀው አጥቅተውታል፣ ታግለውታል፤ ሊያጠፉትም ጥረዋል። ኢሕአፓን ለይቶ የመነጠልና የማዳከም ዘመቻ ዛሬም ባያባራ ኢሕአፓ የጠላቶቹን ጥቃት መክቶ ከ48 ዓመት በኋላ ትግሉን አጠናክሮ እንደቀጠለ ይገኛል።

ባለፉት ድፍን 48 ረዥም የትግል ዓመታት ኢሕአፓ ከውጭ ብቻ ሳይሆን በውስጡ የበቀሉ አሜኬላዎች ሳይቀሩ ሊያጠፉት ሞክረዋል። ዓላማችንን ቀይረን፤ ለሕዝብ የገባነውን ቃል ኪዳን አጥፈን፤ ለጉልበተኞች ተንንበሰን እንደር ሲሉ፤ አይሆንም ለሕዝብ የገባነውን ቃል ኪዳን አናጥፍም ስላላቸው ከጠላት ወግነው ድርጅታዊ ሚስጢሩንና ጠንካራ አባላቱን አጋልጠውበታል፤ አልሆነላቸውም እንጂ ከጠላት ጋር በጣምራ ዘምተው ሊያዳክሙት ሞክረዋል። ይህ ሁሉ የተቀነባበረና የተቀናጀ የኢሕአፓን ታሪክ የማጠልሸትና ድርጅቱን የማጥፋት ተራ አሉባልታና የፈጠራ ታሪክ ዘመቻ ለአርባ ስምንት ዓመታት ሳያባራ ቢቀጥልም በጠንካራ አባላቱና ደጋፊዎቹ ትግል ዘመቻቸው ሊከሽፍ ችሏል።

የኢሕአፓ የትናንትም ሆነ የዛሬ መሠረታዊ ዓላማው የሆነው የሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ባለቤትነት እንዲሁም ማንነቱና አቋሙ ግልጽና ህያው ሆኖ እነሆ ዛሬም ቀጥሎ ይገኛል። ኢሕአፓ ትናንትም ሆነ ዛሬ ያው ኢሕአፓ ነው። ኢሕአፓ ድርጅታዊ ማንነቱን የጠበቀ፤ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝብ እኩልነት የቆመ፤ ብሩህ ተስፋና ዘላቂ ራዕይ ለሚወዳት እናት አጋሩ የሰነቀ በመሆኑ የትግሉ መራዘም፣ የመሰዋእትነቱ መክበድ፤ የሀገራችን ጠላቶች መረባረብ፤ ዓላማውንና የትግል ቃል ኪዳኑን ሊለውጠውና አቅጣጫውን ሊያስተው አልቻለም። ኢሕአፓ የትግል መሰረቱ የሆነውን አልፋና ኦሜጋ ኢትዮጵያዊነቱን ተላብሶ በትግሉ ጸንቶ መቀጠሉ የህዝብ ወገኖችን ያኮራ ጠላትን ያሳፈረ መሆኑን በረዥሙ የትግል ታሪኩ በተግባር አስመስክሯል።

አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ዓመት ሲተካ ኢሕአፓ በአርባ ስምንት ዓመት የትግል እድሜው ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶችና የከፈለውን ታላቅ መስዋዕትነት፤ ያካባተውን የትግል ተመክሮና ትግሉን ለማጎልበት የወሰዳቸው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያው አቅዋሞቹ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ሲገመገም ፤ ዛሬም እንደትናንትናው የትግል መስመሩን ጥራት ያሳየበት፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ የሕዝብ ወገንተኛነቱን ያስመሰከረበትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶችና የፖለቲካ እንክርዳዶችን ያሳፈረና ያሸማቀቀ በትግል ውጣ ውረዱ ተመክሮን ያካበተ የፖለቲካው የበላይነቱን ይዞ የቀጠለ ድርጅት መሆኑ ትናንትም በተጨባጭ የታየ ዛሬም እየተደገመ ያለ ሐቅ ነው።

ኢሕአፓ በአገራችን ታሪክ ውስጥ በየዘመኑ የተነሱ አምባገነኖች በጊዜና በቦታ ልዩነት ምክንያት የተለያየ አበቃቀልና የግል ባህርይ ቢኖራቸውም በወል እንዲታዩ የሚያደርጉዋቸው የጋራ ባህርይ አላቸው የሚለውን ፍልስፍና በ48 ዓመት መራራ የትግል ተመክሮው በጽናት የታገለ ፤ ዛሬም በፅናት እየታገለው ይገኛል።

ዛሬ ወዳለችው ሀገራችን ስንመጣ፤ በመላው የሀገራችን ክፍል የጥይት ድምጽ ሳይጮህና የንጹሀን ደም ሳይፈስ ውሎ የሚነጋበትን ቀን ማየት የሰማይን ያህል እርቋል። በወያኔ ተተክሎና ተኮትኩቶ ሥር የሰደደው የጎሳ ግጭት ለተረኞቹ ባለጊዜዎች የበላይነቱን አስረከቦ ከወያኔያውያን የበላይነት ወደ ኦነጋዊ የበላይነት ዞሯል። በሕዝብ ላይ ጥይት እንደ ሙዚቃ ሲጮህ፤ ደም እንደ ጎርፍ ሲወርድ አንዱ ሌላውን ሲከስ ይስተዋላል። ሁሉም ጥፋቱን የሚሰሩት ወንጀሉን የሚፈጽሙት ግን በሕዝብ ሥም ነው። ሕዝቡን ቢለቁት ዳኘነቱን ቢተውለት ግን የበጀውን ጠንቅቆ ያውቃል። ለሕዝብ ቆሚያለሁ የሚል

መንግሥት ፤ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ቡድን እምነቱን በሕዝብ ላይ መጣል ይኖርበታል። ከሕዝብ እየሸሹ እየገደሉና እያሰሩ ስለሕዝብ መናገር ከሐቅ የራቀ ብቻ ሳይሆን ወንጀል ጭምር ነው።

እኛ ዴሞክራሲ ስንል በዋናነት የሕዝብ ልዕልና ይረጋገጥ ማለታችን ስለሆነ መብት የተሸራረፈበት እንደገና እመቃ የሰፈነበት የሥልጣን ሕጋዊነት ማጠየቂያ ጠብመንጃ ኃይል የሆነበት ሥርዓት ይቀጠል አለማለታችን መሆኑ መታወቅ የአለበት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፤ ለአገራችን ይበጃል የምንለውን የመፍትሄ ሀሳብ ወይም የፖለቲከ አማራጭ የማቅረብ መብታችን የማይገደብ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል ማለታችን ጭማር ነው።

ዛሬም በሕዝብ ጫንቃ ላይ ራሱን ለማደላደልና ለመንገሥ እየተንደረደረብን ያለው አዲሱ ሹም ልክ እንዳለፉት አምባገነኖች ሁሉ ሕዝብን ለማግባባትና የውዴታ ድጋፍን ለማግኘት ፈጽሞ አይጨነቅም። ሕዝብን ለመደለልና ለማታለል ፤ ያየውን እንዳላየ ፤ የሰማውን እንዳልሰማ፤ የተናገረውን እንዳልተናገረ ለማጭበርበር ሳይታክት እየሠራ ለመሆኑ ምስከር መቁጠር ወይንም መጽሐፍ መግለጥ አይጠበቅብንም።

የሹሙ ፍላጎቱና ምኞቱ የሕዝብን ድጋፍ ማትረፍ ሳይሆን ሕዝብን ሰጥ ለጥ አድርጎ እንዴት የሥልጣን መንበሩን ማስጠበቅ ነው። አምባገነኖች የውዴታ ድጋፍ መጠየቅን፤ መተቸትን፤ በሀሳብ ያለመስማማት መብትን፤ የተለየ ሀሳብ መምረጥንና ማማረጥን ይጠሉታል፤ ይሸሹታል ፤ ይፈሩታል። ከየትኛውም የኅብረተሰብ ከፍል ይውጡ ይህ ለአምባገነኖች የሬት ያህል የሚመር ሐቅ ነው። ሕዝቡ አውቆ ተወያይቶ ፤ ተችቶና አመዛዝኖ በነፃ እንዲመርጥ አይፈልጉም። መነሻ እምነታቸው ሁልጊዜ ሕዝብ ተገዥ ነው፤ ደንቆሮ ነው፤ በተፈለገበት ሊጫንና ሊነዳ የሚገባ ነው የሚል ነው። ምንም እንኳ አምባገነኖች ሥልጣናቸው እስኪደላደሉ እስከተወሰነ ወቅት ድረስ ዴሞክራሲያዊ መስለው ቢቀርቡም እውነተኛ ባህሪያቸው ማለትም አፋኝነታቸው፣ ሁሉንም አዋቂ ነኝና እኔን ብቻ ስሙኝ ባይነታቸውና ጨፍላቂነታቸው በአጭር ጊዜ ፈጦና አግጦ ይወጣል። የተቹ ይታደናሉ። የተቃውሙ ዘብጥያ ይወርዳሉ። በደርጉም በወያኔም ታይቷል። በአዲሱ ሹምም በተጨባጭ በስፋት አየታየ ያለው ይኸው ነው።

በሕዝብ ላይ የተጫኑ አምባገነኖች ሁሉ ያዋጣል ባሉበት ቀላምደዋል፤ ልምድ ሆኖባቸውም ቀጥፈዋል ፤ ተጻራራዎቻቸውን ቀሰ በቀስ ቀንሰዋል፤ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ሰርገው ገብተው ከፋፍለዋል፤ አዳክመዋል፤ መሪዎቻቸውንና አባሎቻቸውን አስረዋል፤ አሳደዋል፤ አስቃይተዋል፤ ደብዛቸውን አጥፍተዋል። የሰብዓዊነት ህሊናም ሆነ ሥነ-ምግባር ከቶም አልፈጠረባቸውም። ትናንት ያየነው ዛሬም በአገራችን በገሀድ እየተፈፀመ ያለው ድርጊት የሚያሳየን ነገር ቢኖር ይህንኑ ጸያፍ ድርጊታቸውን ነው።

ይህ በዘረኛነት የተቃኘና አዕምሮውን ያሳውረ፤ ለቡድናዊ ጥቅምና ለራስ ሥልጣን ጥማት እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላምና አንድነት መልካሙን የማይመኝ የዘረኞች መንጋ በንጹሀን ኢትዮጵያውያን በተለይም በአማራው ላይ እየፈፀመ ያለው ግድያና ማፈናቀል በግልፅ አገራችን ወደጥፋት ጎዳና እያመራች ለመሆኑዋ የማይታያቸው ካሉ ሹምና ከሹሙ ጋር ያበሩ ወይም ለሹሙ ያጎበደዱ ብቻ ናቸው።

አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ሲተካ በአዲስ የትግል መንፈስ ያለፈው የጨለማ ዘመን እንዳይቀጥል ማድርግ ኃላፊነቱ የሕዝብ መሆኑም መታወቅ ያለበት ነው። የይስሙላ ዴሞክራሲን በተገቢው ትግል በማጋለጥ ለሐቀኛ ዴሞክራሲና ለሕዝብ

ልዕልና መቆም ያሻል። መብትን የሚለግሥ አገዛዝ የለም - መብት የሕዝብ ትግል ውጤት ነውና። ስለሆነም ሕዝቡ መብቱን ለማስከበር አንድነቱን እያጠናከረ መንግሥት ነን ባዮች አምባገነኖች የነጠቁትን ድምፁን፣ ልዕልናውን፣ መብቱንና የሥልጣን ባለቤትነቱን ማስመለስ ይኖርበታል። ከላይ የተጠቀሰው እንዲሆን ደግሞ የግድ የሀገር ሉዓላዊነት እንዴትና በምን መልክ ሊጠበቅ ይችላል? ይህንንስ ለማድረግ ከማን ጋር ሆኖ?፣ ምንንስ አሟልቶ መጓዝ ይገባል? ሰላም ሰፍኖ፣ የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ፣ የሀገር ሉዓላዊነት በውል እንዲከበር ከሀገር ወዳዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል? …ወዘተ የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ማንሳት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ የሆነ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ጭምር የሀገር ወዳድ ዜጎች ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ የግድ የሚልበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ፣ የሀገር ሉዓላዊነት በሚያስተማምን ደረጃ የሚጠበቅበትን መላ ሳያውቁና ሳያበጁ የሀገር ሉዓላዊንትን ለመጠብቅ ይረዳሉ፣ ካለፈው ይሻላል …. እየተባሉ የሚሰነዘሩ "መፍትሔዎች" በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሳሳቡ እስከሆኑ ድረስ ስበቱ እየጦዘ ሄዶ መበታተን ሊያስከትል እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው።

አሮጌው ዓመት አልፎ መስከረም ሲጠባ በሥሙ እየማሉና እየተገዘቱ መልሰው እሱኑ ሲያስፈራሩትና ሲገድሉት፣ ሲያስርቡትና ሲያፈናቅሉት መኖራቸውን አውቆና ተረድቶ ሕግና ሥርዓት ሲጣስ፣ ሰብአዊ መብቶች ሲጨፈለቁና ፍትህ ሲጓደል ዝም ብሎ ካየ "ከትናንቱ ምን ተማረ?" ያሰኛልና ከተጠናወተን ሕመም ለመፈወስ መድኅኒቱ በአዲስ ዓመት በአዲስ የትግል መንፈስ ጥንካሬን ተላብሰን፣ ከፍርሃት ተላቀን እውነትን ለመናገር የሚደፍር አዕምሮና ልሳን፣ አምባገነኖችን የሚታገል ቆራጥ ወኔ ሊኖረን ይገባል።

ሕዝብንና አገርን የሚጎዳ ስብዕናን የሚነካ እና የሚያዋርድ ተግባር በአጋርና በሕዝብ ላይ ሲፈፀም እያየን ዝም ከማለት ለፍትህና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መነሳት ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድና ለታሪክ በጎ ነገር ትቶ ለማለፍ ይረዳልና በአዲሱ ዓመት በአዲስ የትግል መንፈስ አገራችንና ሕዝባችንን በጋራ እንታደግ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ ድሉን ይቀዳጃል!